## በረከት ስምኦን ከኢሕአዴግ ዋና ፀሃፊነ  ቸው ተሰናበቱ

ከግንቦት 1990 ዓ.ም የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት አንስቶ የኢሕአዴግ ሎጀስቲክስ መምሪያ  ላፊና የፓርቲው ዋና ፀሃፊነትን ተረክበው ሲሰሩ የቆዩት አቶ በረከት ስምኦን ከ ላፊነ  ቸው ተባረዋል:: በምትካቸው የኦሕዴድ አባል የሆኑት አቶ ሙክ  ር ከድር የኢህአዴግ ዋና ፀሐፊ መሆናቸውንም   ማኝ የዜና ምንጮቻችን አረጋግጠዋል:: ይህ ሹም ሽር ይፋ የተደረገው ባለፈው ቅዳሜ ጥር 21/2002 ዓ.ም 3 ሺህ የኢህአዴግ ካድሬዎች በናዝሬት «ጨፌ ኦሮሚያ» ስብሰባ በተካሄደበት ወቅት ነው::
«የምርጫ ሥነ ምግባር» በሚል በናዝሬት በተካሄደው የኢሕአደግ ካድሬዎች ስብሰባ ላይ ለካድሬዎቹ ስልጠና የሰጡት አቶ  ይለ ማርያም ደሳለኝ (ከደኢህዴን)፣ አቶ በረከት ስምኦን (ከብአዴን)  ና አቶ ሙክ  ር ከድር (ከኦህዴድ) ነበሩ:: ስብሰባውን በዋና ቀስቃሽነት የመሩት አቶ ሙክ  ር ከድር በአቶ በረከት ፈን  የኢህአዴግ ዋና ፀሃፊነትን የተረከቡ መሆናቸውን ለ3 ሺህ ካድሬዎች የተገለፀውም በዚሁ የስብሰባ ዕለት ነበር:: ላለፉት ሃያ አምስት ዓመ  ት የኢህአዴግ ሊቀመንበርነት ቦ  ከአቶ መለስ ዜናዊ  ጅ ወጥቶ አያውቅም::
አቶ በረከት በፓርቲ አመራርነ ቸው የመቀጠላቸው ሁኔ  ያከተመለት መሆኑን የሚገልፁ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ኢህአዴግ በምርጫ ወቅትም ላያስመርጣቸው ይችላል የሚል ግም  ቸውን በመግለፅ ላይ ናቸው:: በቅንጅት አባልነት የፓርላማ አባል ለመሆን የበቁት አቶ ልደቱ አያሌው መኖሪያ ክልላቸውን አዳስ አበባ ልደ  አካባቢ ትተው አቶ በረከት ስምኦን በሚወዳደሩበት ቡግና-ወሎ ለመወዳደር መመዝገባቸውን የሚጠቁሙት የዜና ምንጮቻችን አቶ ልደቱ አዲስ አበባ ውስጥ ቢወዳደሩ በሕዝቡ  ንደማይመረጡ ከወዲሁ በመረዳ  ቸው ከምርጫ ሕጉ ውጪ ከኖሩበት 20 ዓመ  ት ወዳለፉቸው ቡግና ወረዳ ሄደው ለመወዳደር መወሰናቸው በኢህአዴግ የተገባላቸው ቃል ሣይኖር  ንደማይቀር ይጠቁማሉ::
በ1992 ዓ.ም ምርጫ ወቅት ፓርላማውን  ንዲያዳምቁ የተፈለጉት የያኔው የግል ተወዳዳሪ አቶ በድሩ አደም በደሌ ወረዳ ውስጥ አብሯቸው  ንዲወዳዳር ተመዝግቦ የነበረው የኢህአዴግ አባል  ንዲነሣላቸው ተደርጎ ብቻቸውን ተወዳድረው  ንዲያሸንፉ መደረጉን ያስ ወሱት የዜና ምንጮቻችን የኢህአዴግን የተለመደ የሸፍጥ አሠራር በማስ ወስ አቶ ልደቱ ፓርላማውን  ንዲያዳምቁ ሲባል በመጨረሻው ሠዓት ቡግና ውስጥ አብረዋቸው የሚወዳደሩትን አቶ በረከት ስምኦንን ከውድድሩ ውጪ ሊያደርጋቸው  ንደሚችል ይጠቁማሉ:: የአዲስ አበባ ህዝብን በመፍራት ለምርጫ ወደ ወሎ ቡግና ያመሩት አቶ ልደቱ አያሌውም በምትኩ ከኢሕዴግ የሚሰጣቸውን የቤት ሥራ ለመሥራት መስማማ  ቸው ተጠቁሟል::

## ኢሕአዴግ 75 ሺህ ወጣቶችን ለስለላ አሠማርቷል

ከአዲስ አበባ አስሩም ክፍለ ከተሞች የተውጣጡ 75 ሺህ የኢህአዴግ አባላት ባለፈው ማክሠኞና ረቡዕ ጥር 25  ና 26 በከተማው በሚገኙ የተለያዩ አዳራሾች ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን፣ በመዝጊያው ዕለት ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ የ2 ሠዓት ቪዲዮ ኮንፈረንስ በመስጠት ፖለቲካዊ ትዕዛዝ ሠጥተዋል:: ኢህአዴግ በጥቅሣ ጥቅም ያሠራቸው ወጣቶች መጪውን የ2002 ምርጫ በተመለከተ ከጠ/ሚኒስትሩ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ተግባራዊ  ንዲያደርጉ ማሣሠበያ የተሠጠበት ስብሰባ መሆኑን የዜና ምንጮቻችን ገልፀዋል::
በቪዲዮ ኮንፈረንሱ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባስተላለፉት ትዕዛዝ ያለፈው የምርጫ ግርግር  ንዳይደገም ወጣቶች በየአካባቢያቸው ንቁ ክትትል በማድረግ በተቃዋሚ ፓርቲ አደራጅነት ስለሚንቀሳቀሱ ወገኖች መረጃ አሠባስበው ለ ናት ድርጅቶቻቸው ማስተላለፍ  ንደሚገባቸው በመግለፅ በይፋ ግለሰቦችን ሳይቀር መሠለል  ንደሚገባቸው ነግረዋቸዋል::
«የቅንጅትን የአድማ ተግባር በዱላ ቅብብል ለማሳካት የተዘጋጁ አካለት ሕልማቸውን ወደ ተግባር ለመለወጥ  የተፍጨረጨሩ መሆኑን የፀጥ  ኀይሎች በተግባር

ደርሰውብ ል» በማለት ለ75 ሺህ ተሠብሣቢ ወጣቶች የተናገሩት አቶ መለስ ዜናዊ «... ነዚህ ይሎች ያለ የሌለ ይላቸውን አሠባሥበው ቀደም ሲል ችግር ባልነበረበት የትግራይ ክልል ጭምር ሁከት ለመፍጠር የሞከሩ መሆናቸውን ተረድ ችሁ በየአካባቢው የሚደረገውን ንቅስቃሴ በመከ ተል ለድርጅቶቻችሁና ለበላይ አካል የፀጥ መስሪያ ቤቶች ሪፖርት ንድ ደርጉ» በማለት በስለላ ንዲሳተፉ ጋብዘዋቸዋል:: አቶ መለስ ስም ሣይጠቅሱ ውንጀላውን ያቀረቡት በመድረክ አባላት ላይ መሆኑን አስተያየት ሠጪዎች ይስማማሉ::

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተዘጋጅቶ በሁለቱ ቀናት ስብሰባ ለወጣቶቹ መወያያ ሆኖ የቀረበው ባለ 25 ገፅ የመወያያ ፅሁፍ ከውስጥ አዋቂዎቻችን የተላከልን ሲሆን፣ በዚህ «የምርጫ አጀንዳችን» የሚል ርዕስ በተሰጠው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፅሁፍ ላይም ተቃዋሚዎች ላይ የበረ ጫና ለማድረግ ዝግጅት የተካሄደ መሆኑም ተጠቁሟል:: በጠ/ሚኒስትሩ ተፅፎ ለኢሕአዴግ አባላት በተበተነው ፅሁፍ ውስጥ ዒላማው የተነጣጠረው በተቃዋሚዎችና በአመራሮቹ ላይ መሆኑን ከሚጠቅሱት መልዕክቶች የሚከተሉት ይገኙብ ል:-

«... ንደሚ ወቀው ሁሉ ድርጅ ችን (ኢሕአዴግ) ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ ነው ብሎ በጥብቅ ያምናል:: አገራችን በብሄር በሃይማኖት ወዘተ በ ጅጉ የለያየ ህዝብ አብሮ የሚኖርባት አገር ነች:: ነዚህን ልዩነቶች በብቃት ማስተናገድ ከቻልን ልዩነቶቹ የጥንካሬያችን ምንጭ ሆነው በሰላምና በመተባበር አገራችንን ከድህነት ማላቀቅና መገንባት ንችላለን:: ልዩነቶችን በብቃት ማስተናገድ ካልቻልን ግን በልዩነቶቻችን ዙሪያ የተናቆርን ለከፋ ብጥብጥና ልቂት መዳረጋችን አይቀሬ ይሆናል::»

«...ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚሰሩት ስራ ብዙውን ጊዜ ጅግ የሚያበሳጭና ልህ አስጨራሽ ንደሆነ ጥርጥር የለውም:: በ ንደዚህ አይነት ተግባር የሰማሩ ሰዎችን አሳዶ በህግ ማስቀጣት ንጂ የምን መብት ማክበር ነው የሚል ስሜት ቢፈጠርም የሚገርም አይሆንም::»

«..በኢትዮጵያ ያሉ ተቃዋሚ ይሎች ሁሉም በኪራይ ሰብሳቢነት ዙሪያ የሚ ዩ ቢሆኑም የየራሳቸው የተለያየ ባህሪ ንዳላቸው የማይካድ ጉዳይ ነው:: አንዳንዶቹ በጠባብነት ዙሪያ ሲሽከረከሩ ሌሎቹ በትምክህኝነት ዙሪያ የሚያሽከረክሩ ናቸው:: ጥቂቶች ለህጋዊና ሰላማዊ ትግል ተገዢ ለመሆን ቆርጠው የተነሱ የሚመስሉ ሲሆኑ ሌሎቹ ለአመፅና ነውጥ የቋመጡ፣ የተቀሩት ደግሞ ንደነገሩ ሁኔ ካንዱ ወደሌላው ሊሸጋገሩ የሚችሉ ናቸው:: ይህንን ስትራቴጂ በምንቀይስበት ወቅት መነሻ የምናደርገው የአመፅና የብጥብጥ አቅጣጫ የሚከተሉትን ቢሆንም ሁሉም ትኩረት ውስጥ ሊሆኑ ይገባል:: ይህንን የምናደርግበት ምክንያት ምንም ንኳን በአሁኑ ወቅት ብዙዎቹ ፓርቲዎች ለህግና ለሰላም ተገዢ ንሆናለን ብለው ቃል ቢገቡም በምርጫው ሂደት የሚደቀኑ ፈተናዎችን ሁሉ በተግባር አልፈው በቃላቸው የሚፀኑ ለመሆናቸው ተጨባጭ ተግባራዊ ማረጋገጫ ግን የለም:: ሆኖም አንዳንዶቹ ትግሉ ከረር ሲል ቃል ከገቡለት ሰላማዊ ትግል ተንሸራተው የአመፅን ጎራ ሊቀላቀሉ ቢችሉ የሚል ጥያቄም ይነሳል:: ይህ ከሆነም የአመፅ ይሉ አሁን ካለው አቅም የተወሰነ ጭማሪ ሊያገኝ ይችላል::»

«... ዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ዋናው ጉዳይ ምንም ንኳ ለብጥብጥ መጠቀሚያ የሚሆኑ ይሎች በርከት ያለ ቁጥር ንዳይኖራቸው ማድረግ ጅግ አስፈላጊ ቢሆንም ዋናው ጉዳይ ነዚህን የሚመክት የህዝብ የተደራጀ ይል መኖር አለመኖሩ ነው:: ለምሳሌ በአንድ ሶሶት ሺህ ተማሪዎች ባሉበት ትምህርት ቤት ውስጥ ሰላሳ የሚሆኑ በጥባጮች ካሉና የተቀረው ተማሪ ተበ ትኖ ምንም የማያደርግ ዛቢ ቢሆን ሰላሳዎቹ ትምህርት ቤቱን በጠቅላላ ያላንዳችን ጥርጥር ማተራመስ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ግን ሰላሳዎቹን ሊመክቱ የሚችሉ 300 የተደራጁና ጠንካራ ተማሪዎች ካሉ ነዚህ ተማሪዎች ሌላውን ተማሪ በማነሳሳት ሰላሳዎቹ በጥባጮች አርፈው ንዲቀመጡ

በቀላሉ ሊያስገድዷቸው ይችላሉ:: ከዚህ አኳያ ወሳኝ የሚሆነው በቀላሉ የማይገመት ቁጥር ያላቸው የብጥብጥ መሳሪያ የሚሆኑ ሰዎችን ማሰባሰብና ማደራጀ ቸው ብቻ ሳይሆን ነዚህን ሊመክትና ከመጀመሪያው ለማምክንና በ ንጭጩ ለመቅጨት የሚችል ተፋላሚ የህዝብ ሃይል የሌለበት ሁኔ መፍጠር አለመፍጠራችን ነው::»

«...ተቃዋሚዎች በግልፅም ሆነ በስውር የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ በቅርብ ተከ ትለን ማስረጃ መያዝ አለብን:: በተቻለ መጠን ሰነዶችን ለማግኘት መሞከር፣ ድርጊቶችን በቪዲዮና በድምፅ ለመቅረፅ ጥረት ማድረግ አለብን:: ይህ የተሟላና አስተማማኝ መረጃ የማግኘትና ማስረጃ የማሰባሰብ ስራ ቀጥሎ ላለው ስራ ሁሉ የላቀ ድርሻ ስላለው በብቃትና ባለማቋረጥ ሊፈፀም የሚገባው ነው::
ማስረጃውን ከያዝን በኋላ በየደረጃው ሁለት ነገሮችን በአንድ ጊዜ ማድረግ ይገባል:: ማስረጃውን ቶለ ብሎ ለበላይ አካል (ቅጂው) ንዲደርስ ማድረግ የመጀመሪያው ጉዳይ ሲሆን መረጃውን ለህዝብ በሰፊው መዘርጋትና በዘህ ላይ በመመስረት የፈፃሚዎችን ህገ-ወጥነትና በጥባጭነት በተከ ይና ያለማቋረጥ ማጋለጥ:: በየ ርከኑ ያለው አመራር መጠኑን ያለፈ ምንም ርምጃ አውሰድ የለበትም:: ይህንን የምንለው በሁለት ምክንያት ነው:: በመጀመሪያ ከስር ከስር ወንጀለኞችን ወደ ማሰርና ርምጃ መውሰድ ከገባን በተግባራቸው በህዝቡ ፊት በተከ ይ ለማጋለጥ ድል አይኖረንም:: ህዝቡ ከሚያየው ተግባር በመነሳት ምሬቱ የጨመረ ሄዶ ርምጃ ንዲወሰድ አምርሮ የሚጠይቅበት ደረጃ ላይ ማድረስ አንችልም:: ስለሆነም ለዘለቄ ው በማያዳግም መንገድ ማስገወድ የምንችልበት ድል ያመልጠናል:: በሁለተኛ ደረጃ በየ ርከኑ ያለው አመራር ርምጃ ቢወሰድ ርምጃ የሚወሰድበት ዋናው ሃይል ሳይሆን የዚህ ተላላኪ ይሆናል:: በተግባር አህያውን ፈርቶ ዳውላውን ይሆናል:: መሆን ያለበት ግን ዳውላውን ትቶ አህያውን ልክ ማስገባት ነው:: ይህ በየደረጃው በሚወሰድ ርምጃ ሊፈፀም አይችልም:: በአገሪቱ በጠቅላላ የሚሰሩትን ስራ ለበላይ አካል በአፋጣኝ ንዲደርሰው በማድረግ የበላይ አካል ሁኔ ዎችንና ማስረጃዎችን አመዛዝኖ በምርጫው ሂደትም ሆነ ማጠናቀቂያ ላይ የማያዳግም ርምጃ የሚወሰድበት ሁኔ መፈጠር ይቻላል::

«...ይህን አፈፃፀም ካለፈው ምርጫ ጋር ያነፃፀርን ብናየው ፋይዳውን በይበልጥ መገንዘብ ንችላለን:: ባለፈው ምርጫ ህገ-ወጥ ተግባር ሲፈፀም በመድረከ ያለው መዋቅራችን ከአንድ አቅጣጫ ወደ ሌላው የሚላጋባት ሁኔ ነበረው:: በየአካባቢው ህጋዊም ህጋዊም ያልሆነም ክልከላና አስተዳደራዊ ርምጃ የሚወስድበት ሁኔ ነበር:: ይህ ሂደት ለነውጠኞች የማጥላላት ዘመቻ በር ከመክፈት አልፎ ያስገኘው ውጤት አልነበረም:: በሌላ በኩልና በዋናነትም ለነውጠኞቹ ዘመቻ በር ላለመክፈት ሲባል መዋቅሩ የበገነም ቢሆን አይቶ ንዳላየ የሚያልፍበት ሁኔ ነው የነበረው:: በመጨረሻም ነውጡን ስንመክት የመጀመሪያ ሰለባ የሆነው ተራው ደጋፊያቸው ንጂ መሪዎቹ አልነበሩም:: መሪዎች ለፍርድ ቀርበው ሲቀጡም ከበ ች አከላት የቀረበ ምንም አይነት ማስረጃ አልነበረም:: በህዝቡ ውስጥ ሰፊ የማጋለጥ ስራ ሳይሰራ የተወሰደ ህጋዊ ርምጃ ስለነበረ ስራት ሲፈረድባቸው ያለፈው በደል አልፏል ይቅር ተደርጎላቸው ምዕራፉ ቢዘጋ ብሎ የሚያስብ ዜጋ ጥቂት ስላልነበረ ይህንኑ ሳቢ በማድረግ በምህረት የተፈቱበት ሁኔ ተፈጥሯል:: አሁን ያስቀመጥን ያለነው አቅጣጫ ግን ከዚሁ በ ጅጉ የተለየና ባለፈው የተከሰቱትን ችግሮች የማይደግም ነው::»

በመቶ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ንዲገደሉ፣ ሺዎች በ ስር ንዲማቅቁ የተደረገበትን የ1977 ምርጫን «አይተን ንዳላየ ያለፍነው ሁኔ ነው የነበረው» በማለት የሚገልፀው አቶ መለስ ዜናዊ በአዲሱ ፅሁፋቸው አንዳች የምርጫ ግርግር በማይ ይበት በዚሕ ወቅት ለአባላቶቻቸው ያቀረቡት ይሕ መልዕክት የሥርዓቱ አምባገንንነት የቱን ያሕል የከፋ ንደሄደ የሚያረጋግጥ መሆኑን የፖለቲካ ዛቢዎች ይስማሙበ ል::